# የትግል ዓመት በትግል ለማክበር

ግንቦት ያለፈው ዓመት የሕዝብ ድምፅ በወንበዴ አገዛዝ ተዘርፎ መውደቅ የነበረበት የመለስ ቡድን በስልጣን ቀጥሏል። ይህን የበላይነት ለማረጋገጥ የመለስ ቡድን ደም ያፈሰሰ፣ ሺዎችን ያቆሰለና ያሰረ ቢሆንም ራሳቸው ተቃዋሚ ኃይሎች ለዚሁ ገዢ ቡድን በስህተታቸው መርዳታቸው ደግሞ የሚካድ ሃቅ አይደለም። ይህንንም መመርመርና መጪውን ግንቦት በህዝባዊ ተቃውሞ መዘከር ደግሞ የሚጠበቅ ከመሆኑ በላይ ያለፈውን ሂደትና ሁኔታ ማጤን ደግሞ የማያመልጡት ግዳጅ ሆኗል።

ግንቦት 97 የመለስ ቡድን በተለይ በገጠር አጭበርብሬ ምርጫውን አሸንፋለሁ በሚል ሲዝናና በደረሰበት የዱብ ዕዳ ሽንፈት ተደናግጦ በወሰደው የጠራራ ፀሐይ የማጭበርበርና አልፎም የፍጅትና የግፍ እርምጃ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጋልጦ ለደጋፊዎቹና ወዳጆቹ ሳይቀር አሳፋሪ ሆኖ ተከስቷል። ከምርጫው በፊት ተቃዋሚ ኃይሎች ሊተባባሩ ችለው በጋራ የጋራ ፅኑ አቅዋም በመያዝ የምርጫውን ህግና ቦርድ ለማስቀየር ቢጥሩ ኖሮ ሂደቱ ለየት ያለና ለሕዝብም የሚጠቅም ሊሆን እንደሚችልም መገመት ይቻላል። በሁለቱ ስብስቦች ማለትም በህብረትና በቅንጅት የነበረው ፉክክር በጤናማ ጎኑ ለሕዝቡ ንቃትና መነሳሳት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ቢያደርግም ቅንጅቱ አለምንም ለውጠ በመርጫ አስተፋለሁ ማለቱ ደግሞ ለአምባገነኑ የልብ ልብ ሰጥቶት ከህብረት ጋር ጀምሮት የነበረውን ድርድር ለማቋረጥ ሁኔታን እንደአመቻቸለት የታየ ነው። ቀደም ሲልም ተቃዋሚ ኃይሎች በመለስ አገዛዝ ላይ ሽንፈት ቢደርስበትና እንደተጠበቀው ወደ ማጭበርበሩ ቢጓዝ ምን ማደረግ አለብን ለሚለው ጥያቄ በተናጠልም ሆነ በጋራ የሰጡት ምላሽ አልነበረም። ይባስ ብለው የሕዝቡን አመፅ ከመ ጴጥሮስ አናውቀውም ያሉ ሲሆን ታቅዶ የነበረውን የሙት ከተማ አድማ በባዕዳን ተፅዕኖ ለማስቀም መወሰናቸው ደግሞ ሁኔታውን አባብሶታል። ከዚህ ሌላ በተጭበረበረው ምርጫ ዙሪያ የራሱን የአገዛዙን የምርጫ ቦርድ በዳኝነት--ወሳኝነት መቀበላቸው ደግሞ በቁርጠት ላይ ውጋት ሆኖ ጉዳት አድርሷል።

ከሁሉም በላይ ግን ለትግሉ ጎጂ የሆነው በአገዛዙ ላይ የነበረው ብዥታ መሆኑ የሚታወቅ ነው። አረመኔው ቡድን ስልጣኑን ለመንከባከብ እስከየት ድረስ ሊሄድ እንደሚችል ተቃዋሚ መሪዎች ነን ያሉ መገመት አልቻሉም። ከጥቅሙ ሌላ ወዳጅ የሌለውንና ሌሎችን አሳልፎ የሰጠውን ኃያል መንግስትም ደህንነታቸውን ጠባቂ አድግው ወሰዱት። የመለስ ሉጓም ከወደ አሜሪካ የሚመጣ መሰላቸው። ሕዝብ ለወሳኝ ፍልሚያ ተዘጋጅቶ እያለ ከባዕዳን ጋር ተመሳጥረው አውላለ ሜዳ ላይ ጣሉት። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ወርቅን በጭቃ እባብን በጫንቃ ይሉ ዘንድ ለትግሉ አጋር የሚሆኗቸውን ርቀው ከአገዛዙ ጎራ ተሰልፎ የሕዝብን ትግል ማጅራት መቺውን አቀፉ። ይህም መሰሪ ቡድን በተሰጠው ተልዕኮ መሰረት በወሳኝ ወቅት ቅንጅቱን ከዳ።

የህብረቱ መሪ ነን ብለው የነበሩትም ስብስቡን ውሳኔ ጥሰውና ረግጠው ወደ መለስ ዜናዊ ፓርላማ አቀኑ:: ይህ ሁሉ በትግሉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ቢያደርግም ሕዝቡ በቆራጥነት ትግሉን ቀጠለ :: ተቃዋሚ መሪዎችም ወደ አገዛዙ ፓርላማ ተጠቃለን አንገባም በማለታቸው የመለስ ቡድን አዛውንት በሽተኛ ሳይል ሁሉንም ቃሊቲ አሰራቸው:: በሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ወደ ዴዴሳና ብር ሸለቆ--ዝዋይ ተወስደው ፍዳ እንዲቀምሱ ተደረገ :: የኋላ መብራት አብርተን ሁኔታውን ለማየት መጣራችን ለክስ ጣት ቅስራ ሮይሆን ከስህተት ለመማር ነውናም ዛሬ በግንቦት ዓመት በሙሉ ልብ የምንደርስበት ድምዳሜ ተቃዋሚ ኃይሎች ባለመተባባራቸው ትግሉንም ራሳቸውንም ለአደጋ ማጋለጣቸውን ነው:: ይህ ሁኔታ ይለወጣል ብንልም ገና ብዙ ትግልን ጠያቂ መሆኑ ደግሞ መታወቅ ያለበት ነው::

በተደጋጋሚ ልንጠቁም እንደሞከርነው ሁናቴው ሲጠጥር ያላውን ወጥር ነውና ተጨባጩን ሁኔታ በማጤን ከአላስፈላጊ መስዋዕትነት መራቁ መቆጠቡ የግድ ነው:: በዚህም መሰረት በተቃውሞ ሰልፍ የሚደርሰውን መጋለጥና ጉዳት ለመቀነስ የሙት ከተማ አድማን አማራጭ በማቅረብ ፍኖተ ዴሞክራሲ መንገድ ጠቋሚና አብሪ ሆና የተጫወተችውም ግንባር ቀደም ሚና የሚዘነጋ አይደለም:: ይህ የሕዝብ አመፅ ዘዴ ደግሞ በስፋትና በበቂ ዝግጅት ከተካሄደ በአገዛዙ ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳትና ለህዝብ ትግል ደግሞ ሊሰጠው የሚችለው ጠቀሜታም በጊዜ የተጠቆመ እንደነበር ማስታወስ የሚቻል ነው:: ይህ አድማ ግን በስፋትና በበቂ ዝግጅት ገና በበቂና በሚገባ አልተሞከረም:: ምን ያህል የመለስን ቡድን በብርክ እንዳስያዘውና ባዕዳንን ልመና እንደሰደደው ደግሞ ያያነው ነው:: የሕዝብ ጠቅላላ አድማ ለዕብሪተኛ አገዛዝ ማርከሻ መሆኑ በታሪክ የተረጋጋጠ ነው:: ወደ ራሳችን የካቲት 66 መለስ ብንልም በእንዳልካቸው መኮንን የአጭር ጊዜ አገዛዝ ላይ የደረሰውንም ማስታወስ እንችላላን:: ዛሬ አገዛዙ የሚፈቅደው ሰላማዊ ትግል ሊካሄደ ባይችልም--ያበቃለት ቢሆንም-- አገዛዙን የሚያርበተብት ሕዝባዊ ተቃዋ/ሞ ግን ሊከሃስደ ይችላል::

ይህ ግን እውን ለመሆንና ውጤት ለማስገኘት የሚጠይቃቸው የቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለ :: በቂ ዝግጅትን የግድ ይላል:: ህብረትን ይጠይቃል--አድማው የሁሉንም ጥሪና ስምምነት ነፀብራቅ ሆኖ እንዲከሰት:: የአንድ ክፍል ብቻ ሳይሆን የአብዛኛው ህብረተሰብ ተቃውሞ የሚታይበት--የሚከሰትበት መሆን አለበት:: በዚህ አቅጣጫ ተቃዋሚ ኃይሎች ብዙ እየጣሩ መሆኑ ይታያል፤ተተጨባጭ ውጤት ግን ገና አለሁ አላለንም:: ተማሪዎች ዛሬም በተቃውሞ ላይ ናቸው:: ሰራተኛው ህዝብ ሊያጅባቸው ሊደግፋቸው ይጠበቃል:: ሰፊው ሕዝብ በአድማው ተካፋይ መሆን ይኖርበታል:: የትግራይ ተወላጆችም በፀረ መለሱ ትግል ግንባር ቀደም ሚናቸውን መጫወት አለባቸው:: የአገዛዙ ሰራዊትና ደጋፊዎችም በጊዜ ወግድ ብለውት ከህዝብ ጎራ ሊደባለቁም ይጠበቃል:: ገና ብዙ የቅስቀሳና የድርጅት ስራ በአንድነት ኃይሎች ትከሻ ላይ ወድቆ ይታያል:: የጠባብ ብሄርተኛው አገዛዝ ፀረ ኢትዮጵያ ሴራና ድርጊት ገና አላለቀም:: የሀገሪቷ ዕጣ ፈንታ ከደይኑ

አልተሳቀቀም--የኢትዮጵያ ህልውና ከአደጋ አልተገላገለም፡፡ ሁሉም ዜጋ ነቅቶ የመታገል ግዴታ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ መጥቶበታል፡፡

ግንቦት 98 መከበር ያለበት ቀጥሎ ያለውን ትግል በማፋፋም ነው፡፡ የታሰሩት እንዲፈቱ፤ የተሰዉት በሚገባ እንዲዘከሩ ትግሉ መፋፋም አለበት፡፡ ይህ ትግል ደግሞ አድርባዮችና የአገዛዙ ቡችሎች ከሚተክሉት አጥር ውጪ ሆኖ፤ የተገዢነትን ግድግዳና ገደብ ንዶ ሕዝባዊ አመፅን የሚያፋፍም መሆን አለበት፡፡ ነጋ ጠባ ከሕዝብ ጎራ ተቀንጣሹና ዋይ ዋይ ባዩ መብዛቱ-መከሰቱ ማቆም አለበት፡፡ የከፋውና የተገፋው ሕዝብ ሰላማዊ መፍትሄ ሲያጣ፤ መንገዱ ሁሉ ሲዘጋበት በአመቺው ምንገድ ማመፁ ግዴታውና ግዳጁ ነው፡፡ እንዴትና በምን ዓይነት እንደሚታገልም ማንም ባዕድ ሆነ የመለስ አረመኔ ቡድን ሊወስንለት አይችልም፡፡ ስለዚህም አንድ የትግል ዓመት በአመፅ መዘከሩ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ የግንቦት የትግል መዘከሪያ ወቅትም በአርድ አንቀጥቅጥ አድማ አገዛዘቱን ለመወጠር ከወዲሁ ዝግጅት መድረጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ጉዳዩን በተመለከተ ወደፊት በተገቢው መንገድ ዝርዝር መባሉ--መቅረቡ ባይቀርም የትግሉ እሳት ከቶም አልተዳፈነምና ሕዝብ ህብረቱንና አንድነቱን አጠናክሮ አገዛዙን በዘርፈ ብዙ ትግል ሊያራውጥ መነሳት አለበት፡፡ የተቃዋሚ ኃይሎች አባላትና ደጋፊዎችም የሕዝቡን ትግል በሚገባ በማዘጋጀትና በማቀነባባር ረገድ የሚጠበቅባቸውን ሚና  እንደሚጫወቱና የሕዝብን ብሶትም በዚሁ መልክ እንደሚያስተጋቡ ይጠበቃል፡፡ የታሰሩት ሁሉ የሚፈቱት በምላላ ወይም የባዕዳን ጥረት ሳይሆን አገዛዙን በሚወጥር ሕዝባዊ ትግል ነው፡፡ ለተባባሩና ለቆረጠ ትግል አማራጭ የለም፡፡ ትግላችን መፋፋም ያለበት በግድ ነው፡፡

አሸባሪው የመለስ አገዛዝ በህዝብ ትግል ይወገዳል!!

ግንቦት 97 በሕዝባዊ ትግል ይዘከራል!!

ድል የሕዝብ ነው--እናቸንፋለን!!!!

ፍኖተ  ዴሞክራሲ  ዝግጅት ክፍል (ሚያዝያ 4 1998) April 12, 2006